## አዘጋጆች

አብርሃም በዕውቀት
ሞሲሳ መገርሳ
ፈድሉ ሸምሱ

# መግቢያ

ዓመታዊ የኹነት የጊዜ ሰሌዳ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ሥራዎችን በተቀናጀና በተደራጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል ነው፡፡ ኹነቶች መቼ፣ የትና በማን እንደሚከበሩ ከፌዴራልና ክልል የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ተቋማት መረጃዎችን በመሰብሰብ አደራጅቶ ለባለድርሻ አካላት በመስጠት ተናባቢ፣ የተቀናጀ፣ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ተደራሽ ለማድረግ የኹነት የጊዜ ሰሌዳ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚዲያን በአጀንዳ ለመምራትና ወቅታዊና ትክክለኛ የመንግሥት መረጃን ለሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ ኹነቶች መቼ፣ የትና በማን እንደሚከበሩ የተደራጀ መረጃ ያስፈልገዋል፡፡ በዚህ መነሻነት የፌዴራል ተቋማት (ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች) የሕዝብ ግንኙነት የሥራ ክፍሎችን እና የክልልና ከተማ አስተዳደሮችን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን የኹነት መረጃዎች በማሰባሰብ አንድ የተደራጀ ዓመታዊ የኹነት የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቷል፡፡

የኹነት የጊዜ ሰሌዳዉን ለማዘጋጀት የሚመለከታቸዉ የሥራ ክፍሎች በወቅቱ መረጃ አለመስጠታቸው፣ አልፎ አልፎ ትክክለኛ የኹነት ጊዜዉን አለማመላከታው፣ ጉልህና ሀገራዊ ኹነቶች ላይ ከማተኮር ይልቅ የተቋሙን የውስጥ አሠራሮች (የአጋርና ባለድርሻ አካላት መድረኮችን፣ ፎረሞችን፣ የዕቅድ አፈጻጸም መድረኮችን ...) እንደ ኹነት ዐቅዶ የመላክ ክፍተቶች ነበሩ፡፡

አገልግሎቱ እነዚህን ክፍተቶች በማረም የዘንድሮዉን ዓመታዊ የኮሙኒኬሽን የኹነት የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቷል፡፡ ይህንን የኹነት የጊዜ ሰሌዳ በመጠቀም መገናኛ ብዙኃን የተቋማትን ኹነቶች ሀገራዊ ገጽታ አሳብሰዉን በተቀረጹበት አጀንዳ ላይ ተመሥርተዉ ተገቢዉን የሚዲያ ሽፋን መስጠት ይችላሉ፡፡ የሚዲያ ተቋማት እነዚህን ኹነቶች ማን፣ የትና መቼ እንደሚያከብር ተገንዝበዉ አስፈላጊዉን ግንኙነት ለመመሥረት እንዲችሉ ያግዛል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የኹነት የጊዜ ሰሌዳ ሀገራዊ ኹነቶችን በተናበበና በተቀናጀ መንገድ ለመምራትና ኹነቶችን በተመለከተ መገናኛ ብዙኃን ተገቢዉ መረጃ ኖሯቸዉ አጀንዳ አድርገዉ እንዲሠሩበት ዕድል ይፈጥራል፡፡ ኹነቶችን ከመንግሥት አቅጣጫዎችና ወቅታዊ ነባራዊ ኹኔታዎች አስተሳስሮ ለመምራት ያስችላል፡፡

# ዓላማ

ሀገራዊ ኹነቶችን በተናበበና በተቀናጀ መንገድ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች

- ✓ ኹነቶችን በተናበበና በተቀናጀ አጀንዳ እና መልእክት ለመምራት፤
- ✓ ስለኹነቶች አስቀድሞ ባለድርሻ አካላትን ለማሳወቅ፤
- ✓ ኹነቶችን በቅንጅትና ትብብር በማዘጋጀት ወጪ ለመቆጠብ፣

## ከአገልግሎቱ የሚጠበቅ ተግባር

የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ይህንን የ2017 በጀት ዓመት የኹነት የጊዜ ሰሌዳ ሲያዘጋጅ የሚወጣቸዉ ተግባርና ኃላፊነቶች እንዳሉ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ከኹነት የጊዜ ሰሌዳ አንጻር ከአገልግሎቱ ይጠበቃል፡፡

- ✓ ኹነቶቹ የሚዲያ ትኩረት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመኾን የንቅናቄ ዕቅዶችን እንዳስፈላጊነቱ ማዘጋጀት፤
- ✓ ኹነቶቹ ለብሔራዊ ትርክትና ሀገር ግንባታ የበኩላቸዉን ሚና እንዲጫወቱ የሚስችሉ መልእክቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መቅረጽ፤
- ✓ ኹነቶቹ ለሀገር ገጽታ ግንባታና ለቱሪዝም ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና እንዲጎላ ድርሻን መወጣት፤
- ✓ ኹነቶቹን መነሻ በማድረግ ልዩ ልዩ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን አጀንዳዎችን መቅረጽና ብልጫ እንዲኖራቸዉ መሥራት፤
- ✓ ኹነቶች የሚመሩበትና ውጤታማ የሚኾኑበትን ሥርዐት መዘርጋትና መከታተል፤
- ✓ በየዓመቱ የኹነት የጊዜ ሰሌዳዎችን እያዘጋጀ ለሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ናቸው፡፡

# ሐምሌ 2016 ዓ.ም

| | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | | | | |

**ረቡዕ 24/16ዓ.ም -ዓለማቀፍ የሬንጀርስ ቀን**

ቱሪዝም ሚኒስቴር

## ነሐሴ 2016 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

## ረቡዕ ነሐሴ 1 ጀምሮ መሳላ በዓል

በከንባታ ጠንባሮ ዞን በሚገኙ ሦስት ሕዝቦች ማለትም በከንባታ፣ ጠንባሮና ዶንጋ ሕዝቦች ዘንድ የዘመን መለወጫ ኾኖ የሚከበር በዓል ነው።

## ሰኞ ነሐሴ -6/12/2016 ዓ.ም ዓለም አቀፍ የዝሆን ቀን

## ሰኞ ነሐሴ 13 የቡሄ በዓል

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች የሚከበር፡ ፡ በአማራ ክልል ደቡብ ጐንደር ዞን መዲና ደብረ ታቦር ደብረ ታቦርን በደብረ ታቦር ተብሎ በልዩ ኹኔታ የሚከበር በዓል ነው።

## ነሐሴ16-21/2016ዓ፣ም ሻዳይ፣ አሸንዳእና ሶለል በዓል

ሃይማኖታዊ መነሻ እንዳላቸው የሚገለጹና ባህላዊነታቸዉ የጎላ በአማራና ትግራይ ክልሎች ያላገቡ ሴቶች ያለምንም ተፅዕኖ በነፃነት የሚቦርቁባቸውና የሚታጬባቸዉ በዓላት ናቸው።

ቱሪዝም ሚኒስቴር እንዲሁም የአማራና ትግራይ ክልሎች ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች

## ከነሐሴ 27-30/2016 ቶኪቤኣ / ዘመን መለወጫ/

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ በዓል ነው

## ጳጉሜን 2016 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | | | | |

### ከ ጳጉሜ1-5ቀን   የዳንዲ በዓል

በጉሙዝ ብሔረሰብ ዘንድ የሚከበረው  ዘመን መለወጫ በዓል ነው፡፡

### ጳግሜ 1-2 የእንግጫ ነቀላና ከሴ አጨዳ በዓል

ዘመን ሲለወጥ  የሚከወን የልጃገረዶች በዓልና ሥርዐት ነው፡፡ በሰሜን ሸዋ፣ በምሥራቅ
እና ምዕራብ ጎጃም እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ይከወናል፡፡

### ከ ጳጉሜ1-5ቀን   ሽኖዬ እና ጎቤ

ኦሮሚያ ክልል የወጣት ሴቶች እና ወንዶች ጭፈራ የዘመን መለወጫ
ባህላዊ ትውፊቶች በሚመለከት

### ከ ጳጉሜ1-5ቀን   አበባየሆሽ /አበባ ዐየሽ ሆይ/

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመስከረም 1 ዋዜማን ለማድመቅ
የታዳጊ ሴት ልጆች ጭፈራ

### ማክሰኞ ጳጉሜ 5 ቀን ህንግጫ በዓል

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በኮንታ ብሔረሰብ ዘንድ የዘመን መለዋወጫ በዓል ነው፡፡

## መስከረም 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 37 | 28 | 29 | 30 | | |

## ረቡዕ መስከረም 1 ቀን 2017 ዓ.ም ብሔራዊ የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ ቀን

**መስከረም 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ - ያ ሆዴ በዓል**

በደቡብ ክፍሎች ውስጥ ለአንድ ወር በድምቀት የሚከበር የዘመን መለወጫ በዓል ነው፡፡

**መስከረም 5/6 ቀን 2017 ዓ.ም መውሊድ በዓል**

ነቢዩ መሓመድ የተወለዱበት ቀን እስበልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበር በዓል ነው፡፡

**ዓርብ መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ማሽቃሮ ባሮ በዓል**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች የዘመን መለወጫ በዓል ነው፡፡

**መስከረም 13/14 ቀን 2017 ዓ.ም ሸዋል ኢድ በሐረር**

ቱሪዝም ሚኒስቴር

**መስከረም 14 ቀን 2017 ዓ.ም ሄቦ በዓል**

የሄቦ በዓል በየም ብሔረሰብ የሚከበር ድንቅ ባህላዊ እሴት ነው፡፡

**መስከረም ከ14-20 ቀናት 2017 ዓ.ም ጊፋታ በዓል**

በወላይታ ሕዝብ ዘንድ ከአሮጌው ወደ ዐዲሱ ዓመት የመሸጋገሪያ በዓል ጊፋታ ይባላል፡፡

**መስከረም 15 ቀን ጋሮዎሬ**
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ዘመን መለወጫ በዓል

**መስከረም 16 እና 17 ቀን 2017 ዓ.ም ደመራ እና መስቀል**
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በድምቀት ይከበራል። በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ በዓል ነው።

**መስከረም 17 ቀን 2017 ዓ.ም ዮ መስቀላ**
የጎፋ ሕዝብ በታላቅ ድምቀት የሚያከብረው የዘመን መለወጫና የመስቀል በዓል ነው።

**መስከረም 17 ቀን የዓለም የቱሪዝም ቀን**
በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበረው የዓለም ቱሪዝም ቀን በኢትዮጵያም በልዩ ኹኔታ በየዓመቱ ይከበራል።

**ዓርብ መስከረም 17/17ዓ.ም ጎፋ ገዜ በዓል**
የጎፋ ዘን ሕዝብ የዘመን መለወጫ በዓል ነዉ

**ዓርብ መስከረም 17/17 ዓ.ም አይዳ ዮኦ ማስቃላ**
የአይዳ ሕዝብ ዘመን መለወጫ ተብሎ ይከበራል።

**መስከረም 21 ቀን 2017 ዓ.ም የግሸን ደብረ ከርቤ ንግሥ በዓል**
በደቡብ ወሎ ዞን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበር ዓመታዊ የንግሥት በዓል ነው። በሚሊዮን የሚቈጠሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ምዕመናንና ጎብኝዎች ይደሙበታል።

**መስከረም 25 እና 26 2017 ዓ.ም እሬቻ በዓል**
የኦሮሞ ሕዝብ ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርብበት ሆራ ፊንፊኔና ሆራ አርሰዲ ላይ የሚደረግ በዓል ነው። አዲስ አበባ አስተዳደር፤ ኦሮሚያ ክልል፤ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከሕዝብ ጋር በዓሉን ያከብሩታል። በዓለም ቅርስነት የተመዘገበ በዓልም ነው።

**ማክሰኞ መስከረም 28/17 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ስደተኛ አዕዋፋት ቀን**
ቱሪዝም ሚኒስቴር

## ጥቅምት 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

**ሰኞ ጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን፤**

**ቅዳሜ ጥቅምት 15 ቀን 2017 ዓ.ም** ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በዳግማዊ ዓፄ ምኒሊክ ዐዋጅ የተቋቋሙበት ቀን (መከላከያ፣ ውጪ ጉዳይ፣ ገንዘብ፣ ፍትሕ ሚኒስቴሮች)

**እሑድ ጥቅምት 24 ቀን 2017 ዓ.ም** በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ሰሜን ዕዝ ላይ በሕወኃት (ወያኔ) ጥቃት የተፈጸመበት ቀን።

## ኅዳር 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

**ኅዳር 2017 ዓ.ም ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ**
በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ቋሚ ባልኾነ ቀን ኅዳር ውስጥ የሚካሄድ ታላቅ ውድድር ነው።

**ሰኞ ኅዳር 16/17 ቀን 2017 ዓ.ም የነጭሪቫን ቀን**
መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

**ዓርብ ኅዳር- 27/17 የፀረ-ሙስና ቀን**
በኢፌዴሪ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስተባባሪነት ይከረበራል።

**እሑድ ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም**
ኅዳር 29 ቀን 2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቀን (የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ነው። በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት በመላዉ ኢትዮጵያ ይከበራል።

**ኅዳር 2017 የዓርብቶአደሮች ልማት ካውንስል**
መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

**ኅዳር 2017 ዓ.ም ዓለም አቀፍ ሕገ-ወጥ የቅርስ ዝውውርን መከላከል ቀን**
ቱሪዝም ሚኒስቴር

**ኅዳር 2017 የሉሲ /ድንቅነሽ የተገኘችበት 50ኛ ዓመት**
ቱሪዝም ሚኒስቴር

**ኅዳር 2017 ቢስት ባር**
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል

## ታኅሣሥ 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

**ማክሰኞ ታኅሣሥ 1 ቀን 2017ዓ.ም ዲሽታ ጊና**
ደቡብ ኢትዮጵያ

**ማክሰኞ ታኅሣሥ 15/ 2017 ማሮ**
ደቡብ ኢትዮጵያ

**ቅዳሜ ታኅሣሥ 26/2017 ዓ.ም**
ዓለማቀፍ የብሬል ቀን

**ማክሰኞ ታኅሣሥ -29/17ዓ.ም የጨለንቆ ሰማዕታት መታሰቢያ**
ሐረሪ ክልል፤ ኦሮሚያ ክልል

**ማክሰኞ ታኅሣሥ - 29/17ዓ.ም የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል**

## ጥር 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኅሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | |

**ከጥር-የካትት 2017 ዓ.ም ደራሮ**
ደቡብ ኢትዮጵያ

**ጥር ሙሉ ወር 2017 ዓ.ም ቱታ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ጥር ሙሉ ወር 2017 ዓ.ም ኦሶማታ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ሐሙስ ከጥር 1-5 ቀናት 2017 ዓ.ም ሾላአ ካሻ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ሐሙስ ጥር 1 ቀን 2017 ዶኦማ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**እሑድ ጥር-11/2017 ዓ.ም የጥምቀት በዓል**
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል ነው፡፡

**ዓርብ ጥር-16 ቀን 2017 ዓ.ም የአፋርኛ ቋንቋ ቀን**
በአፋር ክልል አስተባባሪነት የሚከበር የአፋርኛ ቋንቋ ቀን ነው፡፡

**ዓርብ ጥር 16/2017 ዓ.ም ዓለማቀፍ የትምህርት ቀን**
በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አስተባባሪነት የሚከበር ዓለማቀፍ የትምህርት ቀን፡፡

## ዓርብ ጥር 16/2017 ሀይዞ ህርባ

## ጥርን 2017 ጥርን በባሕር ዳር

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮና ባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር የሚያዘጋጁት ልዩ የጣና ላይ የታንኳ ትርኢት የቱሪስት መስሕብ በዓል።

## ዓርብ ጥር 23/ 2017 ዓ.ም የአገው ፈረሰኞች ማኅበር ዓመታዊ በዓል

አማራ ክልል-አዊ ብ/አስተዳደር፣ እንጅባራ

## እሑድ ጥር 25/2017 የመርቆርዮስ እና ልዩ የፈረስ ጉግስ ትርኢት

አማራ ክልል ደቡብ ጎንደር፣ ደብረ ታቦርና እስቴ መካነ ኢየሱስ

## ረቡዕ ጥር21/2017ዓ.ም አስተርዮ ማርያም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ኹኔታ የሚከበር የማርያም ንግሥ በዓል ና። በአማራ ክልል-ምሥራቅ ጎጃም ዞን መርጡለ ማርያምና በሰሜን ጎንደር ዞን ደረስጌ ማርያም በልዩ ሥርዐትና ድምቀት የሚከበር በርካታ ቱሪስቶች የሚታደሙበት በዓል ነው።

## ጥር 2017 ቲካሻ ቤንጊ

ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

## የካቲት 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | | | | | | |

**የካትት 2017 ፍቼ ጫምባላላ**
ሲዳማ ክልል

**ዓርብ የካቲት 7/2017 ዓ.ም የሬዲዮ ቀን**
ዓለማቀፍ የሬዲዮ ቀን

**ማክሰኞ የካትት 11 ቀን 2017 ዓ.ም ባርባይሳ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ረቡዕ የካትት 12 ቀን 2017 ዓ.ም የሰማዕታት መታሰቢያ**
የጣሊያኑ ፋሺስት አዲስ አበባ ላይ የጨፈጨፋቸዉ የየካቲት 12 ቀን 1933 ዓ.ም ሰማዕታት መታሰቢያ በዓል ነው።

**ረቡዕ የካትት 12/2017 ወናንካ አያና**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ዓርብ የካትት 14/17ዓ.ም የሐረሪ ቋንቋ አፍ መፍቻ ቀን**
በሐረሪ ክልል የሚከበር የሐረሪ ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቀን

**እሑድ የካትት 23 ቀን 2017ዓ.ም የዓድዋ ድል በዓል**
በመለዉ ኢትዮጵያ የሚከበርና የጣሊያን ቅኝ ገዥ ሠራዊት በጀግኖች ኢትዮጵያውያን የተደመሰሰበት ብሔራዊ የድል ቀን መታሰቢያ።

**ሰኞ የካትት 24/17 ዓለም አቀፍ የዱር እንስሳት ቀን**
ቱሪዝም ሚኒስቴር

**ቅዳሜ የካትት 29 ቀን 2017 ዓ.ም የዓለማቀፍ ሴቶች ቀን**
በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስባባሪነት የሚከበር ዓለማቀፍ የሴቶች ቀን በዓል።

## መጋቢት 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | | | | |

**መጋቢት 2017 ክልላዊ የባህልና ኪነ ጥበባት ፌስቲቫል**
አማራ ክልል

**ዓርብ መጋቢት 5/17 ዓ.ም የዋዛ ፌስቲቫል**
ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል

**ሰኞ መጋቢት- 22 ቀን 2017 ዓ.ም ኢድ -አልፈጥር**
በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል።

**መጋቢት 24 ቀን 2017 ዓ.ም የሕዳሴ ግድብ መሠረት የተጣለበት ቀን**
ታላቁ የኢትዮጵያ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበትን መጋቢት 24/2003 ዓ.ም መነሻ በማድረግ ሕዝባዊ ድጋፍን ለማጠናከር የሚከበር በዓል።

**መጋቢት 24 ቀን 2017 ዓ.ም የለውጡ መንግሥት እውን የኾነበት ቀን**
መላው ኢትዮጵያውያን በሰላማዊ ትግል አፋኙንና ከፋፋዩን ወያኔ መራሽ የኢሕአዴግ ሥርዐት አስወግደዉ የለውጥ መንግሥት እውን መኾኑ የተበሰረበት ቀን።

**መጋቢት 2017 ረመዳን**
ሰላም ሚኒስቴር

**መጋቢት 2017 የአርብቶ አደሮች ልማት ካውንስል**
መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር

**መጋቢት 2017 የፀረ ሙስና ቀን**
ሰላም ሚኒስቴር

**መጋቢት 2017 የብዝኃነት ቀን**
ሰላም ሚኒስቴር

**ሰኞ መጋቢት-29/17ዓ.ም ሸዋሊድ**
ሐረሪ ክልል

## ሚያዝያ 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

**ሚያዝያ 2017 የመውሊድ በዓል በጀማ ንጉሥ**
አማራ ክልል፤

**ሚያዝያ 2017 ሳማ ሰንበት**
አማራ ክልል ሰሜን ሸዋ፣ ምንጃር ሸንኮራ ወረዳ

**ዓርብ ሚያዝያ 10 ቀን 2017 ዓ.ም ስቅለት**
በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረዉ የኢየሱስ ክርስቶስ የስቅለት በዓል።

**እሑድ ሚያዝያ 12 ቀን 2017 ዓ.ም ትንሣኤ**
በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረዉ የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ በዓል

**ሰኞ ሚያዝያ 27 ቀን 2017 ዓ.ም የዐርበኞች ቀን**
ጀግኖች የኢትዮጵያ ዐርበኞች የዐምሥት ዓመቱን የጣሊያን ወረራ መክተዉ ንጉሠ ነገሥታቸዉ ከግዞት እንዲመለሱ ያደረጉበት የድል ቀን መታሰቢያ።

## ግንቦት 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

**ቅዳሜ ግንቦት 23/2017 ዓ.ም የላብ አደሮች ቀን**

ዓለማቀፍ የሠራተኞች (የላብ አደሮች) ቀን በሚል ብሔራዊ በዓል ኾኖ ይከበራል።

**ረቡዕ ግንቦት 27/2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጀግኖች ዐርበኞች መታሰቢያ**

የዐምስት ዓመቱን የፋሽስት ጣሊያን ወረራ በመመከት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ዐርበኞች ድል መታሰቢያ ብሔራዊ በዓል ነው።

**ቅዳሜ ግንቦት 30/2017 ዓ.ም ኢድ- አል አድሃ (ዐረፋ)**

በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረዉ የኢድ አል አድሃ (ዐረፋ) በዓል

## ሠኔ 2017 ዓ.ም

| እሑ | ሰኞ | ማክ | ረቡ | ኀሙ | ዓር | ቅዳ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

**ሰኞ ሰኔ 23/2017 ዓ.ም ካራ**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ቅዳሜ ሰኔ 28/2017 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የሰላም ሩጫ**
ሰላም ሚኒስቴር

**ሰኔ ወር ሙሉ 2017 ዓ.ም ኪኤል**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል

**ሰኔ ወር ሙሉ 2017 ዓ.ም ኤክሞሞር**
ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል